# የዕፅዋት አዳቃይ መብት ረቂቅ መመሪያ የዝግጅት ሂደት፣ ማብራሪያ እና አስፈላጊነት

ግብርና ሚኒስቴር

ታሕሳስ/ 2013

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የዕፅዋት አዳቃይ መብት ከአዕምሮአዊ ንብረት መብት እንደ አንዱ የሚቆጠር ሲሆን፤ የዚህ መብት ጥበቃ በተመሳሳይ ከኢኮኖሚያዊ ልማት ጋር ትስስር ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የዕፅዋት አዳቃይ መብት በምርታማነት ዕድገት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ አለው፡፡ ይህን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማስገኘት ሲባል አዳዲስ ዝርያዎችን ከውጭ የማስገባት አስፈላጊነት በቅድሚያ የሚነሳ ጉዳይ ሲሆን ዝርያወን ያፈለቁ አዳቃዮች ከግኝታቸው ተጠቃሚ ሚድረግ ባለመብቱን እና በዘርፉ የተሰማሩትን ለአዳዲስ ግኝቶች ከማነሳሳት ባላፈ እነደ ኢትዮጵያ ላሉ በምግብ ራስን ለመቻል ከፍተኛ ጥረት ለሚያደርጉ ሀገራት የሚያስገኘው ጥቅም የጎላ ነው፡፡

በተጨማሪም ከዚህ አዋጅ በፊት የነበረው የዕፅዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር 481/1998 ከነባራዊና ከአለም አቀፍ አሰራር እና ሁኔታዎች ካለመጣጣም በላይ የማስፈፀሚያ ደንብና መመሪያ ሳይወጣለት በመቅረቱ ሥራ ላይ ሳይወል በአዋጅ ቁጥር 1068/2010 እንዲተካ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በመነሳት በአገር ወስጥም ሆነ በወጪ አገር አዳዲስ የፈለቁ የዕፅዋት ዝርያዎች ጥበቃ ለሚድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ አስራር በማዘርጋት ጥቅም ላይ እንዲወል የእጽዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር 1068/2010 መወጣቱ ይታወቃል፡፡ በዚህ አዋጅ ወስጥ ደንብና መመሪያ በማውጣት አዋጁን ማስፈፀም እንደሚገባ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አዲስ የወጣው አዋጅ ተመሳሳይ እጣ ፋንታ እንዳይገጥመው ለሚድረግ እና በአዋጁ የተሰጠወን ተግባር እና ኃላፊነት በአግባቡ ማስፈፀም እንዲቻል ለወጣው የዕፅዋት አዳቃይ መብት አዋጅ ማስፈፀሚያ ዝርዝር የአፈፃጸም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ ይህንን ረቂቅ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ሠነድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

1. የዕፅዋት አዳቃይ መብት ረቂቅ መመሪያ የዝግጅት ሂደት

## 1.1. የአርቃቂ ኮሚቴ ስለ ማዋቃር፤

የረቂቅ መመሪያው ለማዘጋጀት በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የተለያዩ የሙያ ስብጥር ያላቸው ባለሙያዎች በማደራጀት ስራው እንዲጀመር የተደረገ ሲሆን በዚህም መሠረት ኮሚቴው የሚከተሉትን አባላት እንዲይዝ ተደርጎ ተቋቁሟል፤-

- ከሕግ ዳይሬክቶሬት አንድ ባለሙያ
- ከዝርያ ምዝገባ፣ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ሁለት ባለሙያ
- ከግብርና ምርምር አንድ ባለመያ
- ከዘር ማኅበር አንድ ባለሙያ
- ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ሦስት ባለሙያዎችና
- ከዕፅዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት አንድ ባለሙያ በመሆን ኮሚቴው ተቋቁሞ ረቂቅቅ ደንቡ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. የምክክር አወደጥናት ስለ ማካሄድ

የዕጽዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ለማዘጋጀት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለሞያዎች የተሰባሰቡትን ግብዓቶችና ሌሎች ተጨማሪ ሃሳቦች ከአርቃቂ ኮሚቴ አባላት ተጨምሮበት ሰፋ ባላ መድረክ ቀርቦ እንዲተችበት የምክክር አወደጥናት ተዘጋጅቶ ግብዓት ተሰባስቦ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በዚህ የምክክር መድረክ የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካለት እንዲገኙና እንዲሳተፉ ተደርጓል፤ የተሳታፊዎች ዝርዝርም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ከፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ
- ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
- ከኢትዮጵያ ብዝኃ ሕይወት ኢንስቲትዩት
- ከኢትዮጵያ ምርምር ካወንስል
- ከተቀናጀ የዘር ሴክተር ልማት ፕሮጀክት
- ከዓዕምሯዊ ሃብት ጥበቃ ባለሥልጣን
- ከዘር አምራቾች ማኅበር
- ከግል እና የመንግስት የዘር አምራቾች
- ከግብርና ሚኒስቴር የተለያዩ ዳይሬክቶሬቶች
- ከክልል ግብርና ቢሮዎች እና ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ተቋማት
- ከክልል የምርምር ኢንስቲትዩቶች
- ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች
- ከዓለም አቀፍ የስንዴና በቆሎ ምርምር ተቋማት ተሳትፈወበታል፡፡

ተሳታፊዎች በዋናነት ከአዋጁ ጋር መጣጣም፣ ከዓለም አቀፍ አሰራር ጋር ስላለው አንድነትና ልዩነት በተለይም በኢትዮጵያ ደረጃ መተግበር በሚያስችል ሁኔታ ስለማዘጋጀቱ ትኩረት ሰጥተው ተወያይተውበታል፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ አጠቃቀምንና ግልጽነት እንዲላበስ በማድረግ በኩል ግብዓት ሰጥተውበታል ይህም እንዲካተት ሆንዋል፡፡

### 1.3. የተቋሙ የበላይ አሜራርና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት ለማድረግ የተከናወነ ሂደትን በተመለከተ፡ –

- ✓ የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት እንዲሰጥበትና እንዲዳብር ለማድረግ በዘርፉ መካከለኛ አመራሮች ከዚያም የበላይ አመራሩ አስተያየት ሰጥቶበት እንዲዳብር ተደርጓል፤

በአጠቃላይ ረቂቅ ደንቡ አዋጁን ማስፈጸም እንደሚችል ቢያምኑበትም የማስፈፀም ብቃት ያለው አደረጃጀት ካልተፈጠረለትና የሰለጠነ የሰው ኃይል ካልተሟበለት በስተቀር ተግባራዊነቱ እንደቀደምት ሕጎች ሆኖ እንዳይቀር ስጋታቸውን በአፅንዖት በማድረኩ ገልጸዋል፡፡

## 2. የዕፅዋት አዳቃይ መብት አዋጅ ማስፈፀሚያ ረቂቅ መመሪያ አስፈላጊነት ማብራሪያ

ይህ የማብራርያ ክፍል በዋናነት የሚያተኩረው የመመሪያው እያንዳንዱ ክፍል የተደራጀበትን መነሻ እሳቤ በመግለጽ ላይ ነው፡፡ መነሻው ሲብራራ መመሪያው ያስፈለገበት ምክንያት በግልጽ ለሚዳት ፋይዳው የጎላ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በእርግጥ አዋጁ በተረቀቀበት ወቅት ማብራርያ አብሮ ቀርቦ እንደነበር ባይዘነጋም የአዋጁን ይዘት በሚጥስ ሁኔኩ ይበልጥ ማብራርያ መስጠቱ የመመሪያውን አስፈላጊነት እና ቅቡልነት ያጎላዋል፡፡ ረቂቅ መመሪያው ሲቀረፅ የነበረውንን የሃሳብ ፍሜት አንሚያመላከት ተስፋ ይደረጋል፡፡ የሌሎች አገሮችን፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን እና በዋናነት አገራችን የፈረመቻቸውን ስምምነቶችን በማጣቀስ ረገድ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠ ቢሆንም የአዋጁንና አገራዊ አወድንም ለማጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሌሎችን ተቋማት ህጎችንም/ **ለምሳሌ፡ –** የአካባቢ ጥበቃንና የብዝሃ ሕይወት/ በጥንቃቄ በመመርመር ረቂቁ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

## የዕፅዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ ስለሚቀርብበትና ስለሚመራበት ሁኔታ፡-

የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ጥበቃ ለማግኘት ማንኛወም ሰው ማመልከቻ የማቅረብ መብት እንዳለው እና ሊከለከል እንደሚይገባ በማሳየት ሰብዓዊ መብቱ የተጠበቀ መሆኑን ማመላከት በማስፈለጉ እና በማመልከቻ አቀራረብ ቅደም ተከተል የተነሳ ሊፈጠር የሚችልን የሥነምግባር ግድፈትና የደንበኞች መስተጓጎል ሊያስከትል የሚችልን የህግ ክፍተት ለመድፈን ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህ መሠረትም የሚቀርበው ማመልከቻ ይዘት ምን መምሰል እንዳለበት ለአፈፃፀም ግልፅ በሆነ መንገድ በመደንገግ የተመለከተበትና ማመልከቻ የቀርብበት አግባብ በተለያየ አማራጮች ሊሆን እንደሚችል እንዲሁም ሚኒስትሩ የቀረበወን ማመልከቻ የሚሚምርበት አግባብ ተብራርቶ የተደነገገበት ሆኖ እናገኘዋለን **/አንቀፅ 3ን ይመለከታል/**

በመመሪያው አንቀፅ 4 የዝርያ ባሕሪ መግለጫ የሚያሳከት ሲሆን ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘ አሰራርና ኢትዮጵያም በፈረመቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች መሠረት እንዲሆን ተደርጎ በዝርዝር የባሕሪያት ማለያ ተደርገው የተወሰዱትን እንዲይዝ ተደርጎ ተደንግጓል፣

በመቀጠል የአዳቃይ መብት የሚቀርቡ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የማሕበረሰብ ዝርያዎችን በተመለከተ የሚቀርብ የአዳቃይ መብት ጥያቄ የሚስተናገድበት አግባብ እንዴት ሊስተናገድ እንደሚቻል እና ይህም ደረጃ በደረጃ የሚሳን የጥቅም ወይም የመብት መደራረብ ጥያቄ እንዳይኖር መካላከል በሚያስችል መንገድ የሚስተናገድበት አግባብ የሚያመለከት ነው፡፡ **/አንቀፅ 4-6ን ይመለከታል/**

በመንግሥት የምርምር ተቋማት የሚገኙ አዳቃዮች ተጠቃሚነታቸውን በማሳደግ ለምርምር ሥራ ተነሳሽ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ደግሞ ደመወዝ በመጨመር ብቻ ማምጣት እንደማይቻል አሁንም አርሶአሮች ለመንግስት ዝርያዎች እያሳዩት ያለው አነስተኛ መሳብ በቂ ምስክር ነው፡፡ የመንግስት ምርምር ተቋማት ውጤታማ የሆኑ ተመራማሪዎችን ጠብቀው መቆየት የሚችሉትና የግል አዳቃይ ኩባያዎች ትኩረት የማይሰጡኣቸውን የምግብ ዋስትና ፋይዳ ያላቸውን ዝርያዎች ብዜት ማስቀጠል የሚቻለው አቅም ያላቸውን ተመራማሪዎች ከሚያዳቅሉት ዝርያ ሌሎች ተቀጣሪዎች ከሚያገኙት የደመወዝ ጭማሪ ማበረታቻ በተጨማሪ እንዲያገኙ ሲደረግ ነው፡፡ ስለዚህም የውጭም ሆነ የአገር ወስጥ የአዳቃይ ኩባንያዎች አገር ወስጥ እንዲገቡ ሲደረግ ትኩረት የማይሰጡባቸውን ሰብሎች ዝርያ አቅርቦት ለማስቀጠል ለመንግስት ምርምር ተቋማት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ጥበቃ አሰጣጥ እና የሮያሊቲ ክፍያ አፈጻጸም ምን መሆን እንዳለበት ስርዓት ለማዘረጋት የሚችል ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡
በመንግስት ምርምር ተቋማት በኩል የሚቀርብ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥያቄ በተለየ የሚስተናገድበት አግባብ የሚደነግግ ክፍል ሲሆን ይህም በመንግስት ወይም በሕዝብ ሃብት የተደረገን ምርምር በግል ከተደረገው ምርምር በልዩነት የሚታይ ለመሆኑ የተመለከተበት አግባብ ነው፤ **/አንቀፅ 7ን ይመለከታል/**

**ስለ ግዴታ ፈቃድ አሰጣጥ እና እገዳ**

የግዴታ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ አቋሞች አሉ፡፡አንዳንድ አገራት ወይም ማህበራት በሰው የዕጽዋት ዝርያ መብት ላይ የግዴታ ፈቃድ መጣል አያስፈልግም ይላሉ፡፡ በዚህም ማስረት ህጋቸውን ይቀርጻሉ፡፡ አንዳንድ አገራት ወይም ማህበራት /Associations/ ደግሞ ዕጽዋት ማዳቃል መነሻው በመጀመሪያ የማህበረሰብ ሃብት ስለሆነ ባለመብቱ ከማህበረሰቡ በወሰደው ዘረ-መልና ዕውቀት ያገኘውን ዝርያ ማባዛትና መሸጥ ለህበረተሰቡ ጥቅም ሊያወለው ይገባል ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያ የዕጽዋት አዳቃዮች ሕግና ደንቡ የተረቀቁትም የብዝሃ ሕወት ስብጥር ባለቤት የሆነችውን አገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ተከትሎ ነው፡፡ ባለመብቱ ከአቅም እጥረት የተነሳ ካቃተው መንግስት ቀጥታ እርዳታ ባይሰጠውም ምቹ ሁኔታ አንዲመቻችለት በማድረግ እንዲያባዛ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን ማንኛውም መብቱ ሳይጓደልበት የህዝብን ጥቅም ለማስከበር ሲባል በግዴታ ፈቃድ ሥርዓት ማስረት ሌላ ሰው እንዲያባዛው ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ ይህን ወደ ተግባር ለማለወጥ የሚያስችል የማጠበበቂያ ናሙና ዝርያውን ለመብት ጥበቃ ሲያስማዝግብ አንዲያስቀምጥ ይደረጋል፡፡ ማንኛውም አዳቃይ በኢትዮጵያ ለመንቀሳቀስ ይህን ለማድረግ የተስማማ መሆን አለበት፡፡ አርሶአደሮች ዝርያውን መውደዳቸውን ተመልክቶ ባለመብቱ ልዩ ፍላጎቱን በአገሪቱ ላይ ለመጫን እንዳይሞክር ክፍሉ በቂ የህግ ከለላ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ግን ባለመብቱ ሁልጊዜም መብቱን ሙሉ በሙሉ ለማጠቀም በሚፈልግበት ጊዜ የህዝብን ጥቅም ለማሟላት እስከተስማማ ድረስ የማጠቀም መብቱ አይከለከልም፡፡ ስለዚህም ድንጋጌዎቹ ገደብ የተቀማጠለቸውና ለባለመብቱ አንዲያደሉ ተደርገው የተቀረጹ ናቸው፡፡ የግዴታ ፈቃድ የሚጨረሻ አማራጭ አንደሆነ ለማመልከት ተገቢው ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡

ስለዚህ በዚህ ክፍል  የግዴታ ፈቃድ አሰጣጥ፣እገዳ፣የቆይታ ግዜና ሰለሚራዘምበት ስለሚቋረጥ፣ስለሚሰረዝ እንዲሁም የግዴታ ፈቃድ በማስጠቱ ምክንያት ለባለመብቱ ሚከፈል ሰለሚገባው ክፍያ አተገባበር ዝርዝር ሁኔታዎች አዋጁን መሰረት ተደርጎ ተደንግጓል፡፡

ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በአዳቃይ መብት ላይ ገደብ ስለሚጣልበት የግዴታ ፈቃድ እንዲሰጥ ከመወሰኑ በፊት ግዴታ የሚጣልበት ባለመብት በቅድሚያ መብቱን እንዳያጣ የሚበረታታበት አግባብ የግዴታ ፈቃድ ለማግኘት ጠያቂዎች የሚሟሊጡበት መስፈርት የተመለከተ ድንጋጌ ከበመንግስት ምርምር ተቋማት በኩል የሚቀርብ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥያቄ በተለየ የሚስተናገድበት አግባብ የሚደነግግ ክፍል ሲሆን ይህም በመንግስት ወይም በሕዝብ ሃብት የተደረገን ምርምር በግል ከተደረገው ምርምር በልዩነት የሚታይ ለመሆኑ የተመለከተበት አግባብ ያለውን የሚሟከት ነው፤ **/አንቀፅ 8-11ን ይመለከታል/**

የዕፅዋት አዳቃይ መብት በሚሰጥበት ወቅት ግልጽነት ያለው አሰራር ማዘርጋት ስለሚያስፈልግ የሚጠቀመው የመገናኛ ብዙሃን ብዙ አድማጮች ያሉት መሆን አለበት፡፡
ከዚህ የአዋጁ ገዥ ሃሳብ በመነሳት በቀረበ የአዳቃይ መብት ጥያቄ ላይ የሚቀርብ ማንኛውም ተቃውሞ የሚስተናገድበት አግባብና ውሳኔ አሰጣጥ እንዲሁም የበላይ አካል ስለሚያፀናው ወይም ስለሚያሻሽ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን የተመለከተ ይሆናል በመንግስት ምርምር ተቋማት በኩል የሚቀርብ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ጥያቄ በተለየ የሚስተናገድበት አግባብ የሚደነግግ ክፍል ሲሆን ይህም በመንግስት ወይም በሕዝብ ሃብት የተደረገን ምርምር በግል ከተደረገው ምርምር በልዩነት የሚታይ ለመሆኑ የተመለከተበት አግባብ ነው፤ **/አንቀፅ 13ን ይመለከታል/**